<u>የወንጌል ኃይል</u>

<u>በእምነት መኖር (ክፍል 6)</u>

*"የአሁኑ ዘመን ስቃያችን ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀለን ክብር ጋር ሲነፃፀር ምንም እንዳይደል እቆጥራለሁ"*

*(ሮሜ 8፡18)*

የወንጌል መልእክት በእግዚአብሔር ዘንድ የተዘጋጀውንና ወደ ፊት ሊገለጥ ያለውን  ታላቅ ክብር የሚያካትት ነው። ይሄ ተስፋ የቀደሙት ክርስቲያኖች የደረሰባቸውን ስደትና መከራ እንዲታገሱት ኃይል ሆኖአቸዋል። የእነርሱም እምነትና ተስፋ የነደደውን የወንጌል እሳት ለማጥፋት የመጣውን የጠላትን ስራና እቅድ አፈራርሶታል። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ ምእራፍ 6-7 ክርስቲያን ጌታን ለመውደድና ለማገልገል ሊከተለው የሚገባውን መርሆ ሲገልፅ፤   በሮሜ 8፡1-17 ደግሞ ሰው በምድር ላይ በሚኖርበት ዘመኑ በእግዚአብሔር ፊት የተቀደሰ ህይወት ለመኖር የመንፈስን መርሆ መከተል (በመንፈስ መመላለስ) እንደሚያስፈልገው ገልጿል።

እግዚአብሔር የገባው የክብር የተስፋ ቃል ዋነኛና መሰረታዊ የክርስትና ተስፋ ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በህይወቱ ውስጥ የተለማመደውንንና የደረሰበትን ማንኛውንም ከባድ ሁኔታ ሊመጣ ካለው ታላቅ ክብር ጋር በማነፃፀር *“ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀለን ክብር ጋር ሲነፃፀር” (ሮሜ. 8፡18) የሚለው።*

ማንኛውም አማኝ ስለ ክርስቶስ ሲል መከራ እንዲቀበል የግድ ነው። ሆኖም ይህንን መከራ በደስታና በትእግስት  ለማስተናገድ ጌታ የሚያስፈልገውን ፀጋ ይሰጣል። ጌታ ደቀመዛሙርቱን ስለ ስሙ ሲሉ እንደሚሰደዱ ነግሯቸዋል (ዮሐ. 15፡20)። ሐዋርያው ጳውሎስም ከጥሪአችን አንዱ ስለ ክርስቶስ ብለን የምንቀበለው መከራ እንደሆነ ሲናገር *“በክርስቶስ እንድታምኑ ብቻ ሳይሆን ስለ እርሱ መከራ እንድትቀበሉም ይህ ፀጋ ተሰጥቷችኋልና” (ፊል. 1፡29)።* ይህንን ብናደርግ ሊገለፅ ያለውን የክብር ተስፋ እያሰብን ጊዜያዊ የሆነውን ፈተናና መከራ በሃሴት እናስተናግደዋለን *“ምክንያቱም ቃላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር ያስገኛልና” (2ቆሮ. 4፡17)።*

እኛም ሊመጣ ያለውን ክብር እያሰብን ስለ ክርስቶስ ብለን የምንቀበለውን ጊዜያዊውን መከራ የምንታገስበትን ፀጋ ጌታ ለእያንዳንዳችን ይስጠን።